# የኢህአዴግ "እከክልኝ ልከክልህ" ይገታ ይሆን?

## (ዮርዳኖስ ፍትህነገስት)

### *ከህብረ-ብዕር መጽሄት*

ኢህአዴግ 10ኛ ጉባዔውን በመቀሌ ከተማ ለማካሄድ እጫፍ ላይ እንደደረሰ ይታወቃል፡፡ ከዋናው ጉባዔ በፊትም አራቱ ብሔራዊ ድርጅቶች የየራሳቸውን ጉባዔ አካሄደው ይወክሉናል ብለው የሚያምኑባቸውን ወደ መቀሌ ይልካሉ፡፡ መቀሌ ላይ የሚከትሙት ጉባኤተኞችም የግንባሩን ሊቀመንበር ከመምረጥ ጀምሮ ብዙ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የእስከአሁኑ ልምድ እንደሚያመለክተው የግንባሩ ሊቀመንበርም በመጪው ፓርላማ የጠ/ሚንስትርነቱን ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

ይሄ እንግዲህ ሂደት ነው፡፡ ዋናው ቁምነገሩ ያለው ሂደቱ ላይ ሳይሆን በሂደቱ አፈፃፀም ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚሁ ሂደት በሙስና የተጨማለቁና የሀገርን ራዕይ የሚያጨናግፉ ገዝፌው ሊወጡ ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ እንደ ሻማ ቀልጠው ለህገራቸው ብርሃን የሚሰጡ ጀግኖች ሊወጡበት ይችላል፡፡ ስለዚህ ቁልፉ ጥያቄ አካሄዱ በምን አይነት አፈፃፀም መሆን ይገባዋል የሚለው ነው፡፡ የግምገማዎቹ አካሄድ ጥልቀት እና ድፍረት ያለበት ሆኖ "ብስል ከጥሬው" የሚለይበት ይሆናል፤ ወይንስ እንዲሁ እላይ እላዩን ተነጋግረውበት በግርግሩ "ጥሬዎቹ" ተሸፋፍነው ያልፋሉ? የመጀመሪያው እና ብስል ከጥሬ አበጥሮ የሚለየው አካሄድ ከባድ እና አስቸጋሪው ነው፡፡ ነገር ግን ለግንባሩ ጠቃሚው እሱኛው ነው፡፡ ኢህአዴግ መልካም አስተዳዳር በጥልቀት ማስፈን ያቃተው አንዳንድ ከፍተኛ ሹማምንቱ ሳይቀር በሙስና በመዘፈቃቸው ነው፡፡ በአንድ ወቅት አቶ መለስ ለህዝብ ንግግር ሲያደርጉ ህዝቡም በመሀከሉ ያሉትን ሌቦች ያፅዳ እኛም ደግሞ *"የእኛን ሌቦች"* እናጠራለን በማለት ተናግረው ነበር፡፡

ዘንድሮ እያሰጋን ያለው በስም እንጂ በተግባር ድሮ የምናውቀው ያልሆኑ ኢህአዴጎች እየተበራከቱ ማየታችን ነው፡፡

እነዚህ ግለሰቦች እንደ ደርጎቹ እነሱን ያላቆለጳጰሱትን እንደ ጠላት ከመፈረጅ ጀምሮ የሠላ አስተያየት የሰጣቸውን በሙሉ በሚችሉት መንገድ ለማጥቃት የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ ቂመኞች ናቸው፡፡ ከሀገር ጥቅም ይልቅ የግል ስብዕናቸው ጉዳይ ያሳስባቸዋል፡፡ ምንም ጉዳይን የሚለኩት ከራሳቸው ቁመትና ወርድ ጋር እንጂ ከህገራዊ ጥቅም ጋር በመመልከት አይደለም፡፡ ታዲያ የሚያሳዝነው ብሎም የሚያስፈራው ጉዳይ እነዚህ አይነት ግለሰቦች እስከ ከፍተኛው የስልጣን አርከን ድረስ ወጥተው ስንመለከት ነው፡፡

እነዚህ ሹመኞች "ከእኔ ወዲያ ኢህአዴግ" የሚል ውዳሴ ማርያም የሚደግሙ ብቻ ሳይሆኑ በዙሪያቸውም የሚያሰባስቧቸው ሰዎች እነሱ "ዝለሉ!" ሲሏቸው ለምን ብለው የሚሞግቱ ሳይሆን "ምን ያክል ልዝለል?" የሚሉ ደካማዎችን ነው፡፡ በእነዚህ አይነት ስብስብ የሚመራ ቢሮክራሲ ደግሞ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ጠንቅ ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደጀመርነው የኢህአዴግ ቀጣዩ ጉባዔ እንደ እነዚህ አይነት ግለሰቦችን አንገዋሎ የሚተፋ ነው ወይንስ አሁንም እሹሩሩ የሚል? የካንሠር በሽታ የዘር ህዋሳት (cells) በባህሪው የሚያደርገው በዙሪያው ያሉ ጤነኛ የዘር ህዋሳትን እንደ እሱ እያበላሸ በሂደት ሁሉንም ሟች የሚያደርግ ነው፡፡ ካንሰር በሽታ "ጅል" በሽታ የሚባልበት ምክንያት ልክ እንደ እራሱ ሁሉንም የዘር ህዋሳት አበላሽቶ በመጨረሻ ሁሉም በአንድነት የሚሞቱበት መሆኑ ነው፡፡

ኢህአዴግም በውስጡ እያሉ በስም እንጂ በተግባር እሱን የማይመስሉትን ሴሎች ማስወገድ ካልቻለ በሂደት ጤነኛዎችንም መመረዛቸው አይቀሬ ነው፡፡ መጨረሻው ደግሞ ያው ሞት ነው፡፡ የካንሠር በሽታን ለማዳን ሃኪሞች በመድሃኒቶች (chemotherapy) ይሞክራሉ፤ ሌላኛው አማራጭ ደግሞ የተበላሹትን ሴሎች  በጨረር (Radiation) ለመግደል መሞከር ነው፡፡ ሁለቱም አልሳካ ካሉ እና የካንሠር በሽታው በአንድ ቦታ ብቻ ተወስኖ ከተገኘ ያንን የሰውነት አካል ቆርጦ መጣል ግድ ይላል፡፡ በጊዜ ህክምናውን አግኝቶ ከመስፋፋቱ በፊት ካልተደረሰበት ግን የማይቀረውን የሞት ቀን ቆሞ መጠበቅ ይሆናል፡፡

ኢህአዴግም በውስጡ ሆነው ድርጅቱን እንደ ካንሠር እየበሉት ያሉትን "ግምገማ" በሚባል chemotherapy  እና Radiation ሲያስታምም ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ፈውሱን አላገኘም፡፡ ለዚህም እኮ ነው ባለፈው ጉባኤ ላይ መልካም አስተዳደር ማስፈን "የሞትና ሽረት" ጉዳይ ነው ብሎ ሲያበቃ "ሽረቱ" ቀርቶ ወደ "ሞት" ጉዞ የተጀመረው፡፡ ስለዚህም የ"ግምገማ" chemotherapy  ያላዳነውን አካል በቀዶ ጥገና ቆርጦ ወደ መጣል መሄድ ግዴታው ይመስላል፡፡ አለበለዚያ ይሄ እድል አምልጦ የካንሠር በሽታው በሰውነቱ ውስጥ ከተስፋፋ ቀጣዩ ውይይታችን የሚሆነው የመሞቻው ቀኑን መገመት ይሆናል፡፡  መቼስ ቀዶ ጥገና ሲደረግ የተወሰነ  ህመም መኖሩና ጠባሳ መተዉ አይቀሬ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ህይወትን ለማትረፍ የሚከፈል ዋጋ ነው ተብሎ ማየት ይቻላል፡፡

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት በህወሓት ውስጥ መሰንጠቅ አደጋው የተከሰተ ጊዜ በውስጡ የነበረውን ካንሠር እየለመኑ እና እያስታመሙ መቀጠል አንዱ አማራጭ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀዳሚ ተመራጩ እሱ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን ቀዶ ጥገናው ቀላል እንደማይሆን ቢገመትም እነዚህ በግምገማ እና በውይይት አልለወጥ ያሉ የካንሠር ሴሎችን ቆርጠን መጣል አለብን ወደሚል ውሳኔ ተደረሰ፡፡ በድርጅቱ ላይ ቀዶ ጥገናው የተወሰነ ጠባሳ ትቶ ቢያልፍም ዛሬ ላይ ድርጅቱም ሆነ ሀገሪቱ ያሉበትን ሁኔታ ማንም እንደሚመሰክረው ያ ቀዶ ጥገና ተገቢ ነበር፡፡

ዛሬም ኢህአዴግ ለከፍተኛ ቀዶ ጥገና መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ አልድን ያለውና እያመረቀዘ ያስቸገረውን ቆርጦ ለመጣል! ግንባሩ በአሁኑ ጉባኤ ላይ ይህንን ማድረግ ካልቻለ በቀጣይ ይህንንም እድል ማግኘቱ ያጠያይቃል፡፡

ከወራቶች በፊት የተካሄደው የሀገራዊ ምርጫ ውጤት በኢህአዴጎች ዘንድ በተንሸዋረረ መልኩ እንዳይታይ ያሰጋል፡፡ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ድምፁን የሰጠን እንደው "በስራችን ስለወደደን ብቻ ነው" ብለው ከገመቱ የውድቀታቸው "ሀሁ" ተጀምሯል ማለት ነው፡፡ የምርጫው ውጤት መልዕክቶቹ ዥንጉርጉር በመሆናቸው ኢህአዴግ በሰከነ መልኩ ካልተነተነው በስተቀር ወደ የተሳሳተ ድምዳሜ ያደርሰዋል፡፡ እውነት ነው በልማቱም ሆነ

ሠላም በማስፈኑ ረገድ ኢህአዴግ ምስጋና ተችሮታል። ትንሽ የማይባል ድምፅም አግኝቶበታል። ነገር ግን የተበጣጠሰና ብስለት የጎደለው የተቃዋሚ ፓርቲ ስብስብ በመኖሩና መራጩ ህዝብ ተገቢውን አማራጭ በማጣቱ ድምፁን ለኢህአዴግ የሰጠበትም ሁኔታ ነበር። እዚህ ላይ የምናነሳው ቀላል የማይባል ቁጥር ያለው መራጭ ህዝብ ነው። በቀጣዩ ምርጫ ሰከን ያሉ ፓርቲዎች ከመጡና እዚህም ሆነ እዚያ ተበጣጥሰው ያሉት በእነሱ ጥላ ስር ከተሰባሰቡ ኢህአዴግ ብዙ ድምፅ ሊያጣ ይችላል።

በእዚህኛው ጉባዔ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ የተበላሹ አመራሮችን መንግሎ ካላወጣ መልካም አስተዳደር ማስፈን ስለማይችል በቀጣዩ ምርጫ በቁጣ ድምፅ (protest vote) ወደ የተቃዋሚዎች ኮሮጆ ድምፁን የሚያስገባው የመራጭ ህዝብ ቁጥር ቀላል አይሆንም። ይህም ብቻ አይደለም፤ ኢህአዴግ እራሱን ሊያርም ስለሚችል ከእነ ጉድለቱ "ዋስ እንሁነው" በማለት በዚህኛው ምርጫ ድምፅ የሰጠው ህዝብ በሙሉ በከርሞም እንደዚያ ያደርጋል ማለት ሞኝነት ነው። ስለዚህም የአሁኑ ጉባዔ ትርጉም ለኢህአዴግ ከፍተኛ ነው። እንደአለፈው የባህር ዳሩ ጉባዔ የመልካም አስተዳደር የማስፈኑ ጉዳይ "የሞትና ሽረት" ጉዳይ ነው በማለት በመፈክር ብቻ ይለያያል ወይንስ መልካም አስተዳደር ለማስፈን ብቃት የላቸውም ብሎ ያመነባቸውን ቆርጦ ይጥላል?

ኢህአዴግ ያኔ በብላቴናነቱ ዘመን የነበሩት ጉባዔዎቹ በጣም የሰሉ ነበር ይባላል። ቀጣዩ ጉባዔ ከሚካሄድበት ከመቀሌ ከተማ እርቆ ሳይኬድ በእነ ደጀና ይካሄዱ የነበሩት የሰሉ ውይይቶች አረመኔው ደርግን ለመጣል ያስቻሉ ብቻ ሳይሆኑ የሀገሪቷን መፃኢ ተስፋ ብሩህነት ያመላከቱ ነበሩ። በእነዛ ጉባዔዎች ላይ ግን ሽንገላ አያውቁም ነበር … "እከክልኝ ልከክልህ" ብሎ ነገር አይታወቅም ነበር። ከየግላቸው ስብዕና በላይ በሀገር ራዕይ የሚሟገቱበት መድረኮች ነበሩ።

እውት ነው ዛሬ ላይ ጉባዔው የግድ ደጀና ላይ መካሄድ የለበትም። ነገር ግን ደጀናን ወደ መቀሌ … ደጀናንን ወደ ሃዋሳ … ደጀናን ወደ ባህርዳር … ደጀናን ወደ አዳማ … ማምጣት ግድ ይላል። ጉዳዩ የሚተሳሰረው ከቦታ ጋር ሳይሆን ከውስጥ አስተሳሰብ ጋር በመሆኑ የትም ይሁን የትም፤ መቼም ይሁን መቼ የደጀናን መንፈስ በግንባሩ ጉባዔዎች ላይ ማምጣት ያስፈልጋል።

ለኢህአዴግ ትልቅ ዳገት የሆኑበት ተግዳሮቶች መሀከል በዋነኝነት መልካም አስተዳደር ለማስፈን አለመቻሉ እና በህዝብ ግንኙነቱ ዘርፍ ይሄ ነው የሚባል ስራ አለመሠራቱ ነው። የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶችን ከፍ ሲል ስላነሳን በመቋጫው ላይ በህዝብ ግንኙነቱ ዙሪያ እየታዩ ባሉ ተግዳሮቶቹ ላይ ትንሽ ዳሰሳ እናድርግ።

ሚዲያ ለአንድ መንግስት ትልቅ አቅም ነውና በተገቢው መንገድ መጠቀም መቻል አለት። መንግስት ከህዝቡ ጋር ሊገናኝባቸው ከሚችልበት መንገዶች ዋነኛው በሚዲያ በኩል ነው። በብልሀትና በጥልቀት ከተሰራበት ሚዲያ ህዝቡን ከጫፍ ጫፍ ለማነቃነቅ ሊጠቀምበት ይችላል። በትግሉ ዘመን ወቅት የኢህአዴግ የህዝብ ግኑኝነቱ ስራ (ፕሮፖጋንዳው) በጣም ውጤታማ ከመሆኑ የተነሳ ወጣቶች ህይወታቸውን ሳይቀር ለትግሉ እንዲለግሱ የማድረግ አቅም ነበረው። ዘንድሮ የዛን ጫፉን እንኳን አናይም።

ሀገራዊ አጀንዳዎችን በቋሚነት መቅረፅ የሚገባው የመንግስት ኮምንኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ይህ ነው የሚባል ቀጣይነት ያለው ስራ ሲሠራ አናይም፡፡ መንግስት ወደ ህዝቡ ዘንድ ሊያንቀረቁር የሚፈልጋቸው መልዕክቶች በትክክል እንዲደርሱ መጀመሪያ ላይ የማንቀርቀሪያው አቅም እና ብቃት ሊፈተሽ ይገባዋል፡፡

የትምክህት እና የጠባብነት አመለካከቶችን ለመታገል ብሎም ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት፤ የሃይማኖት አክራሪነት አመለካከቶችን ለመታገል፤ የመልካም አስተዳደር እሴቶችን ለማጎልበት እና የመሳሰሉት አንኳር አጀንዳዎችን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማስረፅ ጠንካራ እና ቀጣይነት ያለው የህዝብ ግንኙነት ስራ ይጠይቃል፡፡

እስከአሁን እንዳየነው እየተሠራ ያለው የእሳት ማጥፋት ዘመቻ ነው እንጂ እስትራቴጂ ያለውና ቀጣይነት ያለው አጀንዳ የማስረፅ ሂደት አይደለም፡፡ "የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች" ወቅት ባህርዳር ከተማ ላይ ብሔር ተኮር መሳይ ግጭቶች የታዩ ሰሞን በትምክህተኝነት እና በጠባብነት ላይ ትንሽ ይነገርና ይረሳል፡፡ የሃይማኖት ፅንፈኛነት ጫፍ ረግጦ የደሴው ሼክ ኑር ይማም የተገደሉ ሰሞን በአክራሪነት ላይ ትንሽ ተብሎ እሱም ተረሳ፡፡ በሽብርተኝነት ላይም እንዲሁ…

በህገ-ወጥ ስደትም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ላይ በተመሳሳይ ወረተኛ የሚያስመስሉ ስራዎች ብቻ ናቸው ሲሰሩ የከረሙት፡፡  በተለይ ደግሞ ለእዚህች ሀገር ከፍተኛ አደጋ እየፈጠረ በሚገኘው የሃይማኖት አክራሪነት አጀንዳ ዙርያ እየተሰራ ያለው ስራ በጣም አሳሳቢ ነው፡፡ የዋህቢያ ፅንፈኛ ቡድኖች የአክራሪነት አጀንዳቸውን ቀን ከለሊት እየለቀቁ ባሉበት ወቅት ያንን የተሳሳተ የአክራሪዎች አስተምህሮት በማጋለጡ ረገድ የመንግስት ኮምኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የሚሠራው ስራ ተመጣጣኝ አይደለም፡፡ ይህም ከፍተኛ አደጋ ነው፡፡ በአጠቃላይ አጀንዳ እየቀረፀ በቋሚት የሚሠራ ሌላ ተቋም የሚያስፈልግ ይመስላል፡፡ ጉባዔው ይህንንም ሊፈትሽ ግድ ይለዋል፡፡

እንደ አብነት የመንግስት ኮምኒኬሽን ጽ/ቤትን አነሳን እንጂ ህዝብን የሚያስመርሩ አገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋማት ሊፈተሹ ይገባል፡፡ በአጠቃላይ በመጪው የኢህአዴግ ጉባዔ መሠረታዊ ለውጦች ይጠበቃል፡፡ ይህ መሠረታዊ ለውጥ ለድርጅቱም ሆነ ለሀገሪቷ ትልቅ ፋይዳ የሚኖረው ነው፡፡

ግንባሩ የቀዶ ጥገና ያድርግ ሲባል የታመመውን አካል አስወግዶ ጤነኛ አካል ለመተካት በሚያደርገው ጥረት ውስጥም ልዩ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባዋል፡፡ የሚተካው የሰውነቱ አካል ጤነኛ መሆኑ ካልተረጋገጠ ስራው የቀዶ ጥገና ስራ ብቻ ሆኖ ይቀርና ጉዳዩ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለቀጣዩ ለኃላፊነት የሚያበቃቸውን ሰዎች ማንነት ከወዲሁ በሚገባ ፈትሾ ብቃታቸውንና ለህዝብ ታማኝነታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

ጉባዔው በጥልቀት እራሱን ፈትሾና መርምሮ የሚቆርጠውን ለመቁረጥ ካልተዘጋጀ አይደለም ቀጣዩን GTP2 (የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ለውጥ)  ሊያስፈፅም ይቅርና ባለፈው GTP1 ያሳካቸውን ሊንድ ይችላል፡፡ ቀጣዩ ጉባዔ ለድርጅቱም ሆነ ለሀገሪቷ ትልቅ እንደምታ እንደሚኖረው ስለሚገመት ጉባዔተኛው ለእራሱና ለሀገሪቷ ታማኝ በመሆን ታሪካዊ ውሳኔዎችን እንዲያስተላልፉ ይጠበቃል፡፡